**እስራኤል አገር**
**የትምህርት ሚኒስቴር**
የፈተናው ዓይነት፦ የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት መልቀቂያ ፈተና
የፈተናው ጊዜ፦ የ2017 ዓ.ም. የበጋ ፈተና
**የፈተናው ቁጥር፦ 029284**
አባሪዎች፦ አባሪ ለጥያቄ 6 (ማስታወቂያ)
አባሪ ለጥያቄ 7 (ፎቶዎች)
**ወደ አማርኛ የተተረጎመ (6)**

# የሃይማኖት ታሪክ

## በሪፎርሙ ትርጉም ያለው የማስተማር ዕቅድ መሠረት ለአዲስ ገቢዎች

### በሃይማኖተኞች ት/ቤቶች ለሚማሩ

## ለተፈታኙ የቀረቡ መመሪያዎች

א. ለፈተናው የተሰጠው ጊዜ፦ ሁለት ሰዓት ተኩል።

ב. የፈተናው መዋቅርና ነጥብ አሰጣጥ፦

ይህ ፈተና ሦስት ምዕራፎችን ይዟል።

ምዕራፍ አንድ —(3×13)— 39 ነጥብ
ምዕራፍ ሁለት —(1×22)— 22 ነጥብ
ምዕራፍ ሦስት —(3×13)— 39 ነጥብ
በአጠቃላይ— 100 ነጥብ

ג. ለመጠቀም የተፈቀደ የመርጃ መሣሪያ፦

የውጭ ቋንቋ-ዕብራይስጥ/ዕብራይስጥ-የውጭ ቋንቋ መዝገበ ቃላት።

ד. ልዩ መመሪያ፦

በመልስህ ላይ ተጨባጭ እውነታዎችን አሳይ፥ ጠቅለል ባለ መልስ አታብቃ።

እንደ ንድፍ (טיוטה) መጻፍ የምትፈልገውን በሙሉ (ርዕሶችን፣ የሒሳብ ስሌቶችንና የመሳሰሉትን) በፈተና ደብተሩ ላይ ብቻ፣ በተለዩ ገጾች ላይ ጻፍ።
በእያንዳንዱ የንድፍ ገጽ ላይ "ንድፍ" ብለህ ከላይ ጻፍ። ማንኛውንም ንድፍ በሌላ ወረቀት ላይ ስትጽፍ ከተገኘህ ፈተናህ ውድቅ ሊሆን ይችላል።

**በዚህ ፈተና ውስጥ የፈተናው መመሪያዎች በወንድ ጾታ ቢሆኑም ለወንድም ለሴትም ተፈታኞች ያገለግላሉ።**

**መልካም ዕድል!**

**מדינת ישראל**
**משרד החינוך**
סוג הבחינה: בגרות
מועד הבחינה: קיץ תשע"ז, 2017
**מספר השאלון: 029284**
נספחים: נספח לשאלה 6 (כרזה)
נספח לשאלה 7 (תצלומים)
**תרגום לאמהרית (6)**

# היסטוריה דתי

## על פי תכנית הרפורמה ללמידה משמעותית

## לעולים חדשים

### בבתי ספר דתיים

## הוראות לנבחן

א. משך הבחינה: שעתיים וחצי.

ב. מבנה השאלון ומפתח ההערכה:

בשאלון זה שלושה פרקים.

פרק ראשון—(13×3) — 39 נקודות
פרק שני— (22×1) — 22 נקודות
פרק שלישי—(13×3) — 39 נקודות
סה"כ — 100 נקודות

ג. חומר עזר מותר בשימוש:

מילון עברי-לועזי / לועזי-עברי.

ד. הוראה מיוחדת:

בתשובתך הבא עובדות ואל תסתפק בהערכות כלליות.

כתוב במחברת הבחינה בלבד, בעמודים נפרדים, כל מה שברצונך לכתוב כטיוטה (ראשי פרקים, חישובים וכדומה).
רשום "טיוטה" בראש כל עמוד טיוטה. רישום טיוטות כלשהן על דפים מחוץ למחברת הבחינה עלול לגרום לפסילת הבחינה!

**ההנחיות בשאלון זה מנוסחות בלשון זכר ומכוונות לנבחנות ולנבחנים כאחד.**

**בהצלחה!**

# ጥያቄዎቹ

## ምዕራፍ አንድ (39 ነጥብ)

ከ1-5 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ ሦስቱን መልስ (ለእያንዳንዱ ጥያቄ — 13 ነጥብ)

**1.** በምዕራብ አውሮፓ የይሁዳዊያን ምሁራን እንቅስቃሴ እንዲስፋፋ ያደረገን አንድ መንስኤ **አቅርብ**።
ሞሼ ሜንዴልሶን (משה מנדלסון) የይሁዳዊያን ምሁራን እንቅስቃሴን ለማስፋፋት ያደረገውን አንድ አስተዋጽዖ **አቅርብ**።

**2.** ከተማርካቸው የይሁዳዊያን ድርጅቶች የአንዱ አባላት (በአውሮፓ ወይም በምሥራቅ አገራት) በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበራቸውን ማወላወል/ማመንታት **አቅርብ**።
የዚህ ድርጅት አባላት ያቀረብከውን ማወላወል የተቋቋሙበትን መንገድ **አብራራ**።

**3.** በፖለቲካው ጽዮናዊነት (הציונות המדינית) እና በተግባር-ተኮር ጽዮናዊነት (הציונות המעשית) መካከል ያለውን አለመግባባት **አቅርብ**።
የ"המזרחי" እንቅስቃሴ ድርጅት የተቋቋመበትን ምክንያት **አብራራ**።

**4.** በመስፈሪያ ቦታዎች (מושבות) (1913) የ"מסע הרבנים"ን መነሻ **አቅርብ**።
በዚህ ክስተት በተለያዩ ቡድኖች መካከል ተግባራዊ የሆነውን ትብብር **አቅርብ**።

**5.** ከ1936 – 1939 ባሉት ዓመታት በ"ሃጋና" (ההגנה) እና "ኤጼል" (אצ"ל) መካከል በማሳለፍ/በመታገስ (הבלגה) ወይም በምላሽ/አፀፋ (תגובה) በሚለው ርዕስ ሥር ክርክር ተካሄዶ ነበር።
በዚህ ክርክር የ"ሃጋና"ን አቋም እና የ"ኤጼል"ን አቋም **አብራራ**።
(በአጠቃላይ – ሁለት አቋማት)።

/ገጽ 3 ላይ ይቀጥላል/

## ምዕራፍ ሁለት (22 ነጥብ)

ከ6-7 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ አንዱን መልስ።

**6.** በጥያቄ 6 አባሪ ላይ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት "ወደ ብሪታኒያ ጦር ሠራዊት ውትድርና ግቡ" የሚል ማስታወቂያ ቀርቧል። ማስታወቂያውን አስተውለህ ተመልከት እና በፊትህ ባሉት ሁለት ንዑሳን ላይ መልስ ስጥ።

**ሀ.** በማስታወቂያው መሠረት፣ ወደ ብሪታኒያ የጦር ሠራዊት መግባት ለምን አስፈላጊ እንደሆነ **ጥቀስ**።
ወጣት ይሁዳዊያንን ወደሠራዊቱ እንዲገቡ ለማሳመን ከተጠቀሙባቸው የማስታወቂያው ክፍሎች (רכיבים) ውስጥ ሁለቱን **አቅርብ**።
(11 ነጥብ)

**ለ.** እስከ 1944 ዓ.ም. ድረስ ብሪታንያዊያን ለምን የይሁዳዊያንን ብርጌድ መቋቋም እንደተቃወሙ አብራራ።
በሁለተኛው የዓለም ጦርነት መጨረሻ ለብሪታንያዊያን የውጊያ ጥረት ይህ ብርጌድ ያበረከተውን አስተዋጽዖ **አቅርብ**። (11 ነጥብ)

**7.** በጥያቄ 7 አባሪ ላይ በሾአ ወቅት ከነበሩት የ"קידוש החיים" ዋጋ የተገለጸባቸው ሁለት ፎቶግራፎች ቀርበዋል። ፎቶዎቹን ተመልከት እና በፊት ባሉት ሁለት ንዑሳን ላይ መልስ ስጥ።

**ሀ.** የሕይወት መቀደስ "קידוש החיים"/"የሕይወት መቀደስ" ዋጋ ምን እንደሆነ **አቅርብ** እና በተለይም በ"ሾአ" ወቅት የዚህን ዋጋ አስፈላጊነት **አብራራ**።
ከፎቶግራፎቹ እያንዳንዳቸው ለምን በ"ሾአ" ወቅት ከ"ሕይወት መቀደስ" ዋጋ ጋር ግንኙነት እንዳላቸው **አብራራ**። (እያንዳንዱን ፎቶ ግራፍ ለየብቻ ተመልከት)።
(11 ነጥብ)

**ለ.** "የሕይወት መቀደስ" ዋጋ የሚገለጸው በ"ሾአ" ወቅት ደግሞም በሥነ-ጽሁፍ "שו"ת" (ጥያቄና መልስ) ነው።
በ"ሾአ" ወቅት ራባናቶች በቀረቡላቸው ጥያቄዎች ላይ መልስ ለመስጠት መቋቋም የነበረባቸውን ሁለት ችግሮች **አቅርብ**። (11 ነጥብ)

/ገጽ 4 ላይ ይቀጥላል/

## **ምዕራፍ ሦስት** (39 ነጥብ)

ከ8-12 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ ሦስቱን መልስ (እያንዳንዱ ጥያቄ — 13 ነጥብ)።

**8.** ሽምቅ ተዋጊዎቹ በአንዳንድ "ጌቶዎች" የነበረውን የተቃውሞ (מרד) ጊዜ በተመለከተ የነበራቸውን ጥርጣሬ/ማወላወል **አቅርብ**።
ይህ መጠራጠር ለምን ከ1942 ዓ.ም. ጀምሮ ብቻ እንደተነሣ **አብራራ**።
በጌቶ ቪልና ወይም በጌቶ ዋርሶ ይህን መጠራጠር ተከትሎ የወጣውን/የጸደቀውን ውሳኔ **አቅርብ**።

**9.** ኅዳር 29 ቀን 1947 (כ"ט בנובמבר) የተባበሩት መንግሥታትን ውሳኔ የይሁዳዊያን ሠፈራዎች ለምን በትልቅ ደስታ እንደተቀበሉት **አብራራ**።
በይሁዳዊያን ሠፈራዎች ላይ ያለውን የዚህን ውሳኔ ሁለት ጉድለቶች **አቅርብ**።

**10.** ከተማርካቸው የእስራኤል ጦርነቶች ውስጥ አንዱን **ምረጥ**፦ የስድስቱ ቀን ጦርነት (מלחמת ששת הימים) ወይም የዮምኪፑር/አስተሰርዮ (מלחמת יום הכיפורים) ጦርነት።
የመረጥከውን የጦርነት ስም እና በዚህ ጦርነት ጊዜ ሀገረ እስራኤልን የተዋጓትን ሀገራት ስሞች በሙሉ **ጥቀስ**።
የጦርነቱን ሁለት ውጤቶች **አቅርብ**።

**11.** ከተማርካቸው የወደ እስራኤል አገር መግባት ጉዞ (ዓልያ) ውስጥ አንዱን ምረጥ፦ በአሥራ ዘጠኝ መቶ ሰባዎቹ ዓመታት ከሶቪየት ሕብረት ወደ እስራኤል አገር መግባት (ዓልያ) ወይም በ19 መቶ ሰማኒያዎቹ ዓመታት ከኢትዮጵያ ወደ እስራኤል አገር መምጣት (ዓልያ)።

– ከሶቪየት ሕብረት ወደ እስራኤል አገር መምጣትን ከመረጥክ፦
የዚች አገር ይሁዳዊያን የተቋቋሙትን አንድ ችግር **አቅርብ**።
ለዚህ "ዓልያ" በእስራኤል አገር እና በውጭ ያሉ ይሁዳዊያን ያደረጉትን እንቅስቃሴ **አቅርብ**።

– ከኢትዮጲያ ወደ እስራኤል አገር መምጣትን መርጠህ ከሆነ፦
የዚች አገር ይሁዳዊያን የተቋቋሙትን አንድ ችግር **አቅርብ**።
ለዚህ "ዓልያ" እስራኤል አገር ያደረገችውን እንቅስቃሴ **አቅርብ**።

**12.** ከተማርካቸው የሰላም ስምምነቶች ውስጥ አንዱን ምረጥ፦ ከግብጽ ጋር የተደረገው የሰላም ስምምነት (1979) ወይም ከዮርዳኖስ ጋር የተደረገው የሰላም ስምምነት (1994)።
የመረጥከውን ስምምነት ስም **ጥቀስ**፣ ይህ ስምምነት በዓረቦች በኩል ያለውን ጥቅም እና እስራኤል ያላትን ጥቅም **አቅርብ**። በዚህ ስምምነት ላይ እስራኤል አገር ምን እንድትሰጥ እንደተገደደች **ጥቀስ**።

**መልካም ዕድል!** **בהצלחה!**

መብቱ ለእስራኤል መንግሥት የተጠበቀ ነው።
መገልበጥም ሆነ ማባዛት እንዲሁም ማሳተም በት/ሚኒስቴር ፈቃድ ብቻ ነው።
זכות היוצרים שמורה למדינת ישראל
אין להעתיק או לפרסם אלא ברשות משרד החינוך

## የጥያቄ 6 አባሪ — ለብሪታንያ መከላከያ ኃይል ለመዝመት የሚያስታውቅ አዋጅ

ወደጓደኞችህ ተቀላቀል!

ልጆችህን አድን!




እናት ሀገርህን ጠብቅ!

(ከ፦ http://web.nli.org.il)

ቶሎ ዝመት!

# የጥያቄ 7 አባሪ— የሾአ ወቅት ፎቶግራፎች

## ዋርሶ ማጎሪያ ውስጥ, ልጆች በጋራ መመገቢያ አዳራሽ



ከጉትማን፦ (1999). ሾአ እና ትውስታው ዘልማን ሼዘር ማዕከል, ገጽ 61

## ሎዥ ማጎሪያ ውስጥ መማሪያ ክፍል



**ከድረ-ገጽ**: http://zachor.michlala.edu/inquiry/arch.aps